አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
BIIROO BARNOOTA BULCHINSA MAGAALAA FINFINNEE
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION EDUCATION BUREAU

በየካ ክፍለ ከተማ የወረዳ 9 አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት ራዕይ ጉድኝት ማዕከል

የ6ኛ ክፍል ግብረገብ ሞዴል ፈተና ጥር 2018ዓ.ም

የጥያቄ ብዛት: 40 **የተፈቀደው ሰዓት:- 1 ሰዓት**

መመሪያ አንድ:- <u>ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች ትክክለኛ መልስ የያዘውን በመምረጥ በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ ፃፍ/ፊ</u>::

1. _____ ማለት ድርጊቶችን ከውጤቶች ጋር ማገናኘት ማለት ነው

   ሀ) ሀላፊነት ለ) ሀላፊነትን መወጣት ሐ) ሀላፊነት መውሰድ መ) ተጠያቂነት

2. ለተሳካ ንባብ ከሚከተሉት ምክሮች ውስጥ ትክክለኛው የቱ ነው?

   ሀ) በአልጋ ላይ ሆኖ ማንበብ ሐ) ጸጥ ያለና በቂ ብርሃን ያለው ቦታ መምረጥ

   ለ) በምናነብበት ጊዜ ድምጽ ማሰማት መ) ሳይቆርጡ ለ 5 ሰዓት ማንበብ

3. አጠቃላይ የጽሁፉን ሀሳብ ለማግኘት የምንጠቀመው የንባብ አይነት ምን ይባላል?

   ሀ) የአሰሳ ንባብ ሐ) የዳሰሳ ንባብ (Scanning/Skimming)

   ለ) ዝምተኛ ንባብ መ) የሀረግ ንባብ

4. በንባብ ጊዜ ዋና ዋና ነጥቦችን ለመለየት የሚረዳው ዘዴ የቱ ነው?

   ሀ) ጽሁፍ ላይ ምልክት ማድረግ ወይም ማስመር ሐ) መጽሐፉን መቅደድ

   ለ) በቃላት መሸምደድ መ) ገጾችን መዝለል

5. ከሚከተሉት ውስጥ በደቂቃ አስከ 1000 ቃላት ማንበብ የሚያስችለን የንባብ አይነት የቱ ነው

   ሀ) የዳሰሳ ንባብ ለ) የአሰሳ ንባብ ሐ) መቃኘት መ) የሀረግ ንባብ

6. ከሚከተሉት ውስጥ የግለሰብ ሀላፊነት ያልሆነው የትኛው ነው

   ሀ) እውነት መናገር ሐ) እርስ በረስ መከባበር

   ለ) በጓደኛ አለመቅናት መ) ጎጂ ነገሮችን አለመጠቀም

7. አንድ ሰው በጓደኞቹ ዘንድ ለመወደድ ወይም ለመከበር እንድ ሌሎች ሰዎች ተመሳሳይ ነገሮችን የማድረግ ስሜት

ሀ) በወላጆች የሚሰጥ ግምት ሐ) የግንኙነት ጭት

ለ) የአቻ ግፊት መ) የበዛ ቁርጠኝነት

8. ከሚከተሉት የውሳኔ አሰጣጥ ችሎታዎች ውስጥ ከሁለት ወይም ከዚያ በላይ ሊሆኑ ከሚችሉ አማራጮች መካከል የመምረጥ ሂደት ነው

ሀ) ምክንያታዊ ውሳኔ ለ) ምክንያታዊነት ሐ) ችግሩን መለየት መ) አሳቢነት

9. _____ ችግሩን የመለየት ሂደት እና ተጓዳኝ የመፍትሔ ዘደዎችን ይመለከታል

ሀ) ግብረገባዊነት ለ) አሳቢነት ሐ) ምክንያታዊ ውሳኔ መ) ምክንያታዊነት

መመሪያ ሁለት፡- <u>ከተራ ቁጥር 10- 13 ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ ያለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ መልሱ።</u>

ዘይነብ የቡድን መሪ ሆና ተመድባለች። የቡድኑ አባላት በተሰጣቸው ጊዜ ስራውን አልጨረሱም ነበር። ዘይነብ ራሷን ነጻ ለማውጣት ያልሰሩትን ተማሪዎች መጥቀስ ትችል ነበር፤ ነገር ግን እንደ መሪነቷ ለስራው መዘግየት ሙሉ ኃላፊነት ወስዳ መምህሩን ይቅርታ ጠየቀች ።

10. ዘይነብ ያሳየችው ተግባር በቡድኑ አባላት ላይ ምን ዓይነት ስሜት ፈጠረ?

ሀ) ስራውን እንዲያቆሙ አደረጋቸው

ለ) እንዲያዝኑና ተስፋ እንዲቆርጡ አደረጋቸው

ሐ) አመስጋኝ እንዲሆኑና በርትተው እንዲሰሩ አነሳሳቸው

መ) ሀላፊነታቸውን ችላ እንዲሉ

11. የዘይነብ ተግባር ከእውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት አንጻር ሲታይ፦

ሀ) ለውጤቱ መጥፎም ይሁን ጥሩ ዝግጁ መሆንን ያሳያል ሐ) ግዴለሽነትን ያሳያል

ለ) ስህተትን በሌሎች ላይ ማሳበብን ያሳያል መ) ለሌሎች አለማሰብ

12. መምህሩ የዘይነብን ተግባር ካየ በኋላ ምን እርምጃ ወሰደ?

ሀ) ቡድኑን ቀጣቸው ሐ) ዘይነብን ከኃላፊነት አነሳቸው

ለ) የዘይነብን መንገድ አድንቆ ጊዜ ጨመረላቸው መ) ዘይነብን አባረራት

13. ከዚህ ታሪክ የምንማረው ቁልፍ ቁምነገር ምንድን ነው?

ሀ) ጥፋትን ደብቆ ማለፍ ጠቃሚ ነው ሐ) ስራ ካላለቀ መምህርን መለመን ይገባል

ለ) እውነተኛ መሪ ኃላፊነትን ይወስዳል መ) ጓደኞቿን መጣላት

14. እውነተኛ ደፋር ሰው ተግባራቱን የሚመራው ከምን በመነሳት ነው?

ሀ) ከሌሎች ሰዎች አስተያየትና ይሁታ በመነሳት ሐ) ከራሱ/ከራሷ እውነተኛ አስተሳሰብ በመነሳት

ለ) ሰዎችን ለማስፈራራት ካለው ፍላጎት በመነሳት መ) እንደ ደካማ ላለመታየት ካለው ፍርሃት በመነሳት

15. ከሚከተሉት ውስጥ የእውነተኛ የግብረ ገብ ምሉዕነት ያለው ሰው መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ራስን በሌሎች ቦታ ሆኖ ማየት ሐ) ሁልጊዜ እውነትን መናገር

ለ) ለሚሰራው ስህተት ሌሎችን ተጠያቂ ማድረግ መ) ለሰው ልጆች እኩል ክብር መስጠት

16. የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የግብረገብ እሴት ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ምቀኝነት ሐ) እንግዳ ተቀባይነት

ለ) ለአረጋውያን ክብር መስጠት መ) ለወላጆች ክብር መስጠት

17. ከሚከተሉት ውስጥ ለህግ ተገዥ የሆነ ሰው መገለጫ ባህሪ የሆነው የቱ ነው?

ሀ) የሌሎችን ንብረት ማውደም ሐ) ግብር መሰወር

ለ) ህዝባዊ መመሪያዎችን ማክበር መ) ግጭቶችን በኃይል መፍታት

18. እውነተኛ የግብረገብ ምሉነት ያለው ሰው ከሚከተሉት አንዱን ባህሪ አይኖረውም?

ሀ) ሀቀኝነት ለ) ትሁት ሐ) ሙሰኛ መ) ሃላፊነት መውሰድ

19. የግብረግብ አለመኖር የሚያስከትለው ችግር የቱ ነው?

ሀ) ለራስ ክብር መስራት

ለ) ሙስናንና ብልሹ አሰራር እንዲጠፋ ያደርጋል

ሐ) መጥፎ ተግባራት በማህበረሰቡ መሃል ቢፈፀም ማንም አያስቆምም

መ) ታማኝነት ቅንነትና ፍቅር ይኖራል

20. ለህግ ተገዥ መሆን በማህበረሰቡ ውስጥ ምንን ያሰፍናል?

ሀ) የሰላም እጦት ሐ) የፍትህ እና የእኩልነት ስሜት

ለ) ስርአት አልበኝነት መ) የነፃነት እጦት

21. ከሚከተሉት አንዱ ለህግ ተገዥ የሆኑ ሰዎች ባህሪ ነው?

ሀ) ራስ ወዳድ ናቸው ሐ) የሀገራቸው ህግ ሲጣሥ ዝም ይላሉ

ለ) ለህግ ተገዥ አይሆኑም መ) መብታቸውንና ግዴታቸውን ያውቃሉ

22. ከህግ ተገዥነት የምናገኘው ጥቅም የቱ ነው?

ሀ) ኢ-ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ለ) ሁከትና ብጥብጥ ሐ) ሰላምና ፍቅር መ) ሙስና

23. ከሚከተሉት አንዱ ከህግ ባህሪያት ውስጥ አይመደብም?

ሀ) ተለዋዋጭነት ለ) ቋሚነት ሐ) የፍትህ እጦት መ) ወጥነት

24. ከሚከተሉት ውስጥ ሥለ ህግ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ) ሁሉም ሰው ህግን በገንዘብ መግዛት ይቻላል

ለ) ህግ ጥፋተኛ ያልሆኑትንም ይቀጣል

ሐ) ህጎችን ሁልጊዜ ማክበር ይኖርብናል

መ) ህጎችን ሥናከብር መርጠን መሆን ይኖርበታል

25. የህግ ከለላ የሚሰጠው የህይወት መሰረታዊ ጉዳይ?

ሀ) ሀብት ለ) ሕግ ሐ) የሰላም እጦት መ) ነፃነት

26. ከሚከተሉት ውስጥ የግብረገባዊ ውሳኔ ተግዳሮት ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ) ምክንያታዊነት ለ) የአቻ ግፊት ሐ) የተገደበ ምክንያታዊነት መ) የግንኙነት ግጭት

27. ከሚከተሉት ውስጥ አገልግሎት ሳይሰጡ በተሳሳተ መንገድ ገንዘብ መውሰድ የትኛው የሙስና መገለጫ ነው?

ሀ) ማጭበርበር ለ) ጉቦ መስጠት ሐ) የዝምድና ወገንተኝነት መ) የሰባዊ መብት ጥሰት

28. በስልጣን ላይ ያሉ ግለሰቦች የራሳቸውን ጥቅም ብቻ ሲያሳድዱና የህዝብን መብት ሲጥሱ ምን ይፈጠራል?

ሀ) ሰላም ለ) ሙስና ሐ) ታማኝነት መ) ግልጽነት

29. የሀገርን ደህንነትና ሰላም ለመጠበቅ የዜጎች ሚና ምን መሆን አለበት?

ሀ) ህግን አለማክበር ሐ) ለህግና ለደንብ ተገዥ መሆን

ለ) በህገ-ወጥ ተግባራት መሳተፍ መ) ግዴታን አለመወጣት

30. "ባህሪ በምርጫ የሚመጣ ውጤት ነው" ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ) ባህሪ በተፈጥሮ የሚገኝ ነው

ለ) ሰዎች መጥፎ ወይም ጥሩ ተግባር የመፈጸም የመምረጥ ብቃት አላቸው

ሐ) ምርጫ በባህሪ ላይ ተጽዕኖ የለውም

መ) ባህሪን መቀየር አይቻልም

31. መልካም ባህሪ የሌላቸው ተማሪዎች የሚያጋጥማቸው ችግር ምንድነው?

ሀ) የሌሎችን እምነት ማግኘት ሐ) ጓደኛ አልባ አለመሆን

ለ) በሰዎች ዘንድ መወደድ መ) በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ማጣት

32. ከሚከተሉት ውስጥ የመልካም ባህሪ መገለጫ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ታማኝነት ለ) ክብር መስጠት ሐ) የሌሎችን ንብረት አለማክበር መ) ራስን መቆጣጠር

33. ክብር መስጠት ሲባል ምን ማለት ነው?

ሀ) ለሰዎች ዕውቅና መስጠትና በአክብሮት መያዝ ሐ) ሰዎችን መናቅ

ለ) ሰዎችን መሳደብ መ) በሰዎች ስራ ጣልቃ መግባት

34. መልካም ባህሪ መያዝ በዕለት ተዕለት ህይወታችን ውስጥ ምን ፋይዳ አለው?

ሀ) ህይወታችን አስቸጋሪ እንዲሆን ያደርጋል ሐ) ለስኬታማና ለተከበረ ህይወት መሰረት ነው

ለ) ከሰዎች ጋር እንድንጣላ ያደርጋል መ) ምንም ጥቅም የለውም

35. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መልካም ባህሪን ለማሳየት ምን ማድረግ አለባቸው?

ሀ) የመምህራንን ንግግር ማቋረጥ ሐ) ሁልጊዜ ረብሻ መፍጠር

ለ) የክፍል ደንቦችን መጣስ መ) ጓደኞቻቸውን መርዳትና መከባበር

36. አንድ ሰው በራስ መተማመኑ የሚቀንሰው?

ሀ) አክብሮት ሲኖረው ለ) ሀቀኛ ሲሆን ሐ) ሲሰርቅና ሲያጭበረብር መ) ታማ መሆን

37. _____ ማለት የአንድ ሰው ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱንና ልምዶችን የመቆጣጠር ብቃት ማለት ነው?

ሀ) ለራስ ስሜት መገዛት ለ) ለህግ ተዘዋሪ መሆን ሐ) ደፋርነት መ) ራስን መቆጣጠር

38. _____ በህዝቦች ሥምምነት ላይ ተመርኩዞ በመንግስት አካላት ይዘጋጃል

ሀ) ዜግነት ለ) ምሉዕነት ሐ) ሕግ መ) ተሞክሮ

39. የሀቀኛ ሰዎች መለያ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ፍቅር፣ሞገስ፣ እውነትና ስኬታማነትን ማግኘት

ለ) ለራሱ ዋጋ መስጠት እና ውስጣዊ ጥንካሬ

ሐ) ከጓደኛ፣ ከቤተሰብ እና ከማህበረሰቡ የተገለሉ ናቸው

መ) በቤተሰብ ዘንድ አዎንታዊ ምስል መፍጠር

40 የሀቀኛ፣ ሰዎች መለያ ባህሪ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ) ስህተትን አምኖ መቀበል ለ) የገቡትን ቃል ማክበር ሐ) አለማጋነን መ) እውነት አለመናገር